ለኢትዮጵያ ባሃኢ ማሕበረሰብ በሙሉ

እጅግ የምትፈቀሩ ወዳጆች!

አላህ ኡ አብሃ!

በ177ኛው የባሃኢ ዘመን የመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራት የባሃኢ ዓለም ከተወዳጁ ዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትሕ የተስፋና የእርጋታ ምንጭ የሆኑ ተከታታይ መልዕክቶችን የመቀበል ጸጋ በማግኘቱ ለተባረከው ውበት ምስጋና እያቀረብን፤ የናውሩዝና የሪዝቫን መልዕክቶችን አስከትሎ እ.ኤ.አ በ9 ሜይ 2020 ዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትሕ ለብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባዔዎች በሙሉ አንድ ተጨማሪ መልዕክት መላኩን ለኢትዮጵያ ባሃኢ ማሕበረሰብ በደስታ ለማብሰር እንወዳለን።

ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባዔያችን የእነዚህን ሦስት የዓለም አቀፍ ቤተፍትሕ መልዕክቶች ተያያዥነት በመረዳት እ.ኤ.አ በ9 ሜይ 2020 የተላከውን መልዕክት ሙሉውን ለባሃኢ ማሕበረሰቡ ለማካፈል ወስኗል። ይህ መልዕክት በያዝነው የአምስቱ ዓመት ዕቅድ መገባደጃ ዓመት የሚወጡትን የተቋማት ዕቅዶችና የባሃኢ ማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች የሚመራ፣ ትርጉም ላላቸው አገልግሎቶች ብቅ ማለትም መሠረት የሚጥል መሆኑን በማመን፣ መልዕክቱ በግል እና በቤተሰብ ደረጃ መጠናት እንዲጀመር፣ የመልዕክቱን ይዘት እንዴት ወደ ተግባር ለመለወጥ እንደሚቻልም በጥልቀት እንድናሰላስል ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባዔው ጥሪውን ያቀርባል።

ፍቅር ከተመላው የባሃኢ ሠላምታ ጋር

የኢትዮጵያ ባሃኢዎች<br>
ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባዔ<br>
ግንቦት 2012 ዓ.ም.